# (እግዚአብሔር አስነሣ)

ከሥነ ፍጥረት ጀምሮ ዓለም አሁን እስከደረሰችበት ዘመን ድረስ አገርን እየመሩና ሕዝብን እያስተዳደሩ ያለፉ መሪዎችም ሆኑ አሁን በማስተዳደር ላይ የሚገኙት መሪዎች በአገራቸው ላይ ችግር የሚገጥማቸው እና በሚመሩት ሕዝብ ዘንድ ተደማጭነትን የሚያጡት ፤መሪዎችም የተጠየቁትን እና የሕዝቡን ፍላጎት ከማሞላት አንጻር ተገቢውን መስፈርት አሟልተው ያለመገኘታቸው ሁኔታ የሚፈጠረው ሕዝብና መሪ ተባብረው አገር ለማሳደግ ባለመነሳታቸው ነው። መሪ ያለ ሕዝብ ማስተዳደር ፤ ሕዝብም ያለ መሪ መተዳደር አይሆንለትም። ሕዝበ እስራኤል በሊቀ ነብያት ሙሴ አማካኝነት ምድረ ግብጽን ለቅቀው ከወጡ በኋላ ይወዱትና ይተማመኑበት የነበረው ሙሴ ምድረ ርስትን ሳይረግጥ ሕይወቱ እንደሚያልፍ ስለተነገረው በምትኩ ኢያሱ ወልደ ነዌ የአስተዳደሩን ቦታ ሲረከብ እጅግ አስደሳች ዜና ተሰማ። ሕዝብ ለመሪው ሊገዛ ቃል ገባ ፤ እግዚአብሔርም ከመረጠው የአገር መሪ ጋር «አልጥልህም አልተውህም» ብሎ ቃል ገባ።

ሙሴን ያጡ እስራኤላውያን ከኢያሱ ጋር ቃል የገቡት በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነበር፡- «ያዘዝኸውን ነገር ሁሉ እናደርጋለን ወደምትለንም ስፍራ እንሄዳለን። በሁሉም ለሙሴ እንደታዘዝን እንዲሁ ለአንተ ደግሞ እንታዘዛለን ብቻ አምላክህ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንደ ነበረ ከአንተ ጋር ይሁን።» ኢያሱ ፩፥፲፮-፲፯

ከዚህ በታች የተጻፈው ጽሑፍም አብይ መልእክት እግዚአብሔር በምድር ላይ የተቀባ ንጉሥ እንዲያሥነሳ ነው። ሕዝብና መሪ ተከባብሮ የሚኖርበት ዘመን እንዲመጣ እና እግዚአብሔር ለንግሥና ዳዊትን ካልታሰበ ቦታ መርጦ እንዳስነሣው አሁንም ባለንበት ዘመን እግዚአብሔርን ፈርቶና አክብሮ የሚኖር መሪ ከእግዚአብሔር እንዲመረጥ ነው። ምድር ጸጥ ብላ በሰላም እንድትኖር የሚታዘዝ ሕዝብና በሰላምና በፍቅር የሚመራ መሪ ያስፈልጋል። ተቻችሎ መኖርን ገንዘብ ያደረገ ሕዝብ ምንኛ የታደለ ነው!

## እግዚአብሔር አስነሣ

ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ! አምላከ እስጢፋኖስ
በፊት ለአንተ ስግደት ለንጉሥ ክርስቶስ።
በአንተ ፊት ለመቆም ዕድል የሰጠኸን፣
ከቤትህ ቆመናል ምስጋና ደርድረን።
እንደ አብርሃም ጸሎት እንደ ቆርነሌዎስ፣
ይኼንን መሥዋዕት ተቀበል ክርስቶስ።
በፍርሃት ነው እንጂ በድፍረት አልቆምንም
በአንተ ፊት ክርስቶስ ንጹህ አይደለንም።

በሰናዖር ምድር ቋንቋ ተደባልቆ፣
የአንዱን ነገር አንዱ ለመስማት ተጨንቆ፣
ዓለም ግራ ገብቶት ሲኖር በጥላቻ፣
ቁልፍ ተቸግሮ የምሥጢር መክፈቻ፣
አልሆንልህ ሲለው ተናግሮ መግባባት፣
በዘር መከፋፈል ገንዘብ ሆነው ጥፋት።
በነገድ በጎሳ በቋንቋ በቀለም፣
ሕዝብ ተለያየ የሚኖር በአንድ ዓለም።

አንዱ አንዱን ለመጉዳት አንዱ አንዱን
ለመውረር፣
ሰይፍ ስሎ ማንሳት ጦር ሰብቆ መወርወር፣
የዕለት ግብር ሆኖ ሰልፍ ለጦርነት፣
ብዙ ደም ፈሰሰ በድንጋይ በብረት።

ሰላም አልባ ሆነው የምድር ነገሥታት፣
ምድር ተቃጥላለች በሰው ሰራሽ እሳት።
ፍትህ ተጓደለ የእውነት ፍርድ ጠፋ፣
ሰይፍ ተሰንግሎ ሰው ሰውን አጠፋ።
መከባበር ጠፍቶ መግባባት በወሬ፣
ተበላልቶ አለቀ የሰው ልጅ እንደ አውሬ።
መፍትሔ አልባ ሆኖ ተስማምቶ መኖሩ፣
ሕይወት ትርጉም አጥቶ ሰዎች ተቸገሩ፣
ቋንቋ ጦር ሲያማዝዝ በጸብ ሲያራርቀን፣
አንድ መሆን ከብዶን መግባባት ሲያቅተን፣
አጽናኝ መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሰረጸው፣
በእሳት አምሳል መጥቶ ዓለምን ቀደሰው።
የአንዱን ልሳን አንዱ ይናገረው ጀመር፣
መንፈስ ቅዱስ ወርዶ የሚያስገርም ነገር።

ድንቅ ይገርማል አሉ ተአምራቱን አይተው፣
የተሰበሰቡት ቋንቋቸውን ሰምተው፣
ለዛሬው መገለጽ ትምህርት እንዲሆነን፣
እግዚአብሔር ተገልጸህ በቀደመው ዘመን፣
ሙሴን እንዲያግዙት ሰባ ሰዎች መርጠህ፣
ትንቢት አናግረኻል በመንፈስ አንድ አርገህ

ዛሬም አንድ አድርገን እግዚአብሔር አስማምተህ
የሙሴ ዓይነት መሪ ለምድሪቱ ሰጥተህ።
ሃያ መቶ ዓመታት ብለን እየቆጠርን፣
ዛሬም ሰላም ጠፍቶ እንዴት እንኖራለን።
ዓለም አንድ ያረገ በቋንቋ ያግባባ፣
ዛሬም መንፈስ ቅዱስ ሊመራን ካልገባ፣
በሥርዓት ለመኖር አባት ይከብደናል፣
እጅህ ካልገባበት ዓለም ሰላም ያጣል።

በአንተ ያልተመረጠ አንተ ያልጠራኸው፣
ነብይ አስነስተህ ዘይት ያልቀባኸው፣
ቢፈርድ ያበላሻል ቢመራ አይሰማም፣
እጅህ ከሌለበት ይኼ ዓለም አይለማም።
ይህ ነው ልመናችን ወደ መንፈስ ቅዱስ፣
አምላክ እንዲያስነሣ የተቀባ ንጉሥ።
ዘር ቀለም የማይመርጥ አድልዎ የሌለበት፣
እግዚአብሔርን ፈሪ የተሞላ በእውነት፣

በአንድነት  የሚያምን  ከነገድ ከጎሳ፣
የተቀባ   ንጉሥ   ክርስቶስ   አስነሣ።

ሃይማኖት አክባሪ እግዚአብሔርን ፈሪ፣
«እውቀትና ጥበብ ስጠኝ» የሚል መሪ፣
«ድጋፍ ሁነኝ» ብሎ አንተን የሚያናግር፣
እግዚአብሔር አስነሣ ድንቅ መሪ በምድር
ሥልጣን ገንዘብ አርጎ በሰው ላይ የማይፈርድ፣
ሥርዓት የሚያከብር በሕግ የሚራመድ፣
ሰው ያሻታል ዓለም በቃልህ የሚያድር፣
ፍርድ  የማያዛባ  ሐቅ  የሚመሰክር።

ዕድሜ ልኩን ላይኖር የምድር ሥልጣን ሲመኝ፣
ቀን አይወጣ መስሎት ፍርድ አጣሞ ሲገኝ
ፅንስ  ሲያስጨነግፍ  ሕፃናቱን  ሲገል፣
የደም ጩኸት ሰምተህ ተነሣህ ለበቀል።
በቃ የምትልበት የአንተ ሰዓት አለህ፣
በጦር   የታመነን   በቃል   ትጥላለህ።
«እኔ የሠራሁት የኔ  እጆች  ያበጀው»፣
እያለ ሲመካ «የአባይ ወንዝ የኔ ነው»፣
ዝም ብትል አይቶ ቃልህ እንዲፈጸም፣
ፈርዖን  አሰበ  ከሱ  በላይ  የለም።
ሠራዊቱን  አምኖ  ገንዘቡን  ሥልጣኑን፣
ፈርዖን ዘንግቶት ሞት ድንገት መምጣቱን፣
ማን አለብኝ ብሎ በዕብሪት ሲንቀሳቀስ፣
ወንድ እየመረጠ የሕፃን ደም ሲያፈስ፣
ያኔ ላከው ሙሴን በትር ብቻ አስይዘህ፣
የፈርዖን ትምክህት ባዶ እንደሆን አውቀህ።
ከእረኝነት መርጠህ ክብር ያሳየኸው፣
«ያለ የነበረ  የሚኖር  ነኝ» ያልከው፣
ሰራዊት  ያልያዘ  ብረት ያልታጠቀ፣
በትር ይዞ ገብቶ ንጉሥ አስጨነቀ።
ስንት ዓመት ለኖረ ግብጽን እየገዛ፣
በሕዝበ እስራኤል ላይ አሳር እያበዛ፣
ያልታሰበ   ጥሪ   ያልተዘጋጀበት፣
«ሕዝቤን ልቀቅ» የሚል መልእክት መጣበት።
በመጣበት መልእክት ፈርዖን ራደ፣
መቅረዙ ከስፍራው ድንገት ተወሰደ።
ቃል ብቻ ተናግረህ መልእክተኛ ልከህ፣
እንዲህ የንጉሥ ልብ አባት ታቀልጣለህ።
አንተ ሰው አስነሣ በዘይት ቀብተህ፣
እውቀትና ጥበብ ማስተዋልን ሰጥተህ።
ያኔ  እንጸናለን  ምድር  ትረጋለች፣
አንተ ለመረጥከው ተገዝታ ታድራለች።

አሁን ግን ክርስቶስ ምድር ደም ጠግባለች፣
የእዬዬ የዋይታ የለቅሶ ቦታ ነች።
ሰው ያላሰበውን ክርስቶስ አስነሣው፣
በትሩን ቀብተህ በዙፋን ላይ አውጣው።

ዳዊትን ንግሥና አባቱ አልመረጠው፣
አንተነህ ዙፋን ላይ ጠርተህ ያስቀመጥከው።
«እነግሣለሁ» የሚል ሀሳብ ሳይኖርበት፣
መልእክተኛ አስልከህ ጠራኸው በድንገት።

በአባቱ ፊትማ ዳዊት እረኛ ነው፣
ታናሽ ብላቴና ያልተመረጠ ሰው፣
የተናቀ አንሥተህ እንዲህ ስታከብረው፣
በአባቱ ዓይን ደሃ በአንተ ዓይን ንጉሥ ነው።

የመረጥከው ነቢይ አንተ እንዳልከው ታዞ፣
ንግሥና ሊቀባ ቅብዓ ንጉሥ ይዞ፣
ከእሴይ ልጆች መሃል ሊያነግሥ በእስራኤል፣
ዘይት በቀንድ ይዞ ተገኘ ሳሙኤል።
ኤልያብ ቀረበ ንግሥናው አልሠራም፣
አሚናዳብ መጣ እርሱም አልተቀባም።
እሴይ ሣማን ላከው በሱም ላይ አልሆነም፣
እግዚአብሔር ገና ነው ከ፫ቱ አልመረጠም።
ናትናኤል ራዳይ አሳምም ቀረቡ፣
አምላክ አልፈቀደም ሁሉም አልተቀቡ።
በተርታ ቀረቡ እሴይ ያመጣቸው፣
ሳይደርሳቸው ቀረ ንግሥናው ለአንዳቸው።

በእሴይ ያልታሰበ እሴይ ያልመረጠው፣
ያ ታማኝ እረኛ ከብት የሚጠብቀው፣
ድንገት ተላከበት መልእክት ደረሰው፣
ለካስ ያ ንግሥና ቀድሞም ለዳዊት ነው።

አንተ ካልቀባኸው በአንተ ካልተጠራ፣
ፍርድ አልባ መሪ ነው አገር የሚመራ።
እግዚአብሔር አስነሣ ከቤትህ ባለሟል፣
አንተ ምራኝ የሚል የሚያድር በአንተ ቃል
ስምህን የያዘ አንተን ተሰፋ የሚያደርግ፣
ሰላምን የሚወድ ሕዝብን የሚታደግ፣
እንደ ዳዊት ዓይነት እንባ የተሰጠው፣
እግዚአብሔር አስነሣ አርቆ አሳቢ ሰው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!

ሰኔ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም አብርሃም ሰሎሞን

የሚያባራ ዝናብ መታን ከሚለው መጽሐፍ ላይ የተወሰደ

abraham.solomon@yahoo.com